# ምዕራቡ እና የዲፕሎማሲ ትግል

(ግርማ ሞገስ) girma.moges@yahoo.com

እሮብ፣ ሐምሌ 21 ቀን 2002 (July 28, 2010)

በኢትዮጵያ ለዲሞክራሲ የሚደረገው ሰላማዊ ትግል ሁለት እንቅፋቶች እንዳሉት ግልጽ እየሆነ መጥቷል። አንደኛው ከውስጥ ሲሆን ሁለተኛው ከውጭ ነው። የውስጡ እንቅፋት ዋንኛው እንቅፋት ሲሆን የውጭው እንቅፋት መለስተኛው እንቅፋት ነው። የውስጡ እንቅፋት ሁለት የፖለቲካ ኃይሎች ያከተተ ሲሆን እነሱም በአብዮታዊ ዲሞክራሲ የተሸፈነው የመለስ ዜናዊ ስልጣን ያለመልቀቅ ምኞት እና የተቃዋሚ ድርጅቶች (አንድ አለመሆናቸው) ናቸው። ከውጭ ከገጠሙት እንቅፋቶች ውስጥ ዋንኛው ምዕራቡ ሲሆን ቻይና፣ ኢሳያስ አፈወርቂ፣ አልሸባብ እና ሌሎችም የየበኩላቸውን እንቅፋትነት ማበርከታቸው እየተስተዋለ ነው። **የውስጡን እንቅፋት ወደ ጎን በመተው በዚህ ጽሑፍ የውጭው እንቅፋት (ጠላት) በተለይም ምዕራቡ በሰፊው ይተነተናል።**

## ቻይና፣ ምዕራቡ፣ አልሸባብ፣ መለስ ዜናዊ፥

ቻይና እነ ቪኦኤን በማፈን፣ የፓርቲ ግንባታ ምክሮችን በማካፈል እና መሰል ከንግድ ውጭ በሆኑ የውስጥ ጉዳዮች ጣልቃ በመግባት ለመለስ ዜናዊ መንግስት እገዛዎች በማድረግ በኢትዮጵያ ለዲሞክራሲ በሚደረገው ትግል ላይ እንቅፋት መሆኗ በግልጽ የሚታይ ሃቅ ነው። ከምርጫ 2002 በኋላ ደግሞ ኢትዮጵያ እና ቻይና ወታደራዊ ትብብር ለማድረግም የሁለቱ አገሮች የጦር ሹማምንት ቃል እንደገቡ ቺንዋ (Xinhua) የተባለው በእንግሊዘኛ የሚታተም የቻይና ጋዜጣ ዘግቧል።[①] ይኼ የተደረገው ምናልባት ምዕራቡ በምርጫው ውጤት (99.6%) ተቀይሞ የሰጠኝን ኮንትራት ከነፈገኝ መጠባበቂያ በሚል ወይንም ወደ ቻይና መሄድ እንደሚቻል ለምዕራቡ የማስፈራሪያ መልዕክት ለማስተላለፍ የተደረገ (ፕላን ቢ) ይመስላል።

በምዕራቡ በኩል ደግሞ የቻይና በምስራቅ አፍሪካ መኖር በሽብር ላይ በሚካሄደው ጦርነት ላይ የሚያሳድረው ስጋት ባለመኖሩ የአፍሪካ ቀንድን አልፎም መላ አፍሪካን ከቻይና ጋር በጥንቃቄ ተጋርቶ ለመኖር የመረጠ ይመስላል። ቻይና የመላ አፍሪካን ጥሬ ሃብት በሰፊው በርካሽ በመዝረፍ ላይ መሰማሯን ምዕራቡ የሚያውቀው እና የማይደሰትበት ጉዳይ ቢሆንም የጠቀሜታ መቃቃርን ለጊዜው ወደጎን በማድረግ ምዕራቡ በአልቃይዳ/አልሸባብ ላይ ያተኮረ ይመስላል። ይሁን እንጂ

---

[①] BEIJING, June 28 (Xinhua) -- Senior Chinese and Ethiopian military officials pledged Monday to establish closer relations between the two nation's armed forces.

በምስራቅ አፍሪካ አልሸባብ ቢደመሰስ አፍሪካን አስመልክቶ የምዕራቡ እና የቻይና ግንኙነት ጸባይ ሊቀየር ይችላል።

አልሸባብ ከተደመሰሰ በምስራቅ አፍሪካ ሽብርተኛነት ተደመሰሰ ማለት ነው። ይህ ማለት መልስ ዜናዊን የምዕራቡ ተፈቃሪ (Darling) ያደረገው ምክንያት ተወገደ ማለት ነው። ይኸ ከሆነ ደግሞ የምዕራቡ እና የመለስ መንግስት ግንኙነት ጸባይም ሊቀየር ይችላል። የመለስ መንግስት ግን ለስልጣኑ ሲል በምዕራቡ ዘንድ የተፈላጊነቱ እድሜ እንዲራዘም ሊመኝ ይችላል። ይኸን ምኞቱን ተፈጻሚ ለማድረግ በአደባባይ ሌሎቹን ተቀላቅሎ ስለ አልሸባብ መደምሰስ እየዘመረ በተግባር ግን ይፋ ባልሆኑ የተለያዩ መንገዶች የአልሸባብን እድሜ በማራዘም ተግባር ሊሰማራ ይችል ይሆናል። በኡጋንዳ ካምፓላ አልሸባብ የአለም እግር ኳስ የዋንጫ ጨዋታ ተመልካቾችን ከፈጀ በኋላ አለም በአልሸባብ ላይ ይበልጥ የሰጋ ይመስላል። አልሸባብን ለመደምሰስ ዝግጅት የተጀመረ ይመስላል። የመለስን አኪያሄድ በቅርብ መከታተል ተገቢ ይመስለኛል።

## ኢሳያስ አፈወርቂ፣ የሱዳኑ ዑመር አል-በሽር፣ የጅቡቲው ጌሌ እና አልሸባብ፥

ኢሳያስ አፈወርቂም ኢትዮጵያን ለማዳከም ከነበረው የፖለቲካ ምኞት እና ባድመ ላይ የደረሰበት ሽንፈትን ለመበቀል ሲል አልሸባብን በጦር መሳሪያ እና በሌሎች ጉዳዮች እረድቷል። ኢሳያስ ይህን ሲያደርግ የነበረው አልሸባብ ከአልቃይዳ ጋር የነበረው ግንኙነት አለም እያወቀው ነበር። የኢሳያስ ተግባር ግን ኢትዮጵያን ከመጉዳት ይልቅ አለሸባብ በፍጥነት እንዲያድግ እና በምስራቅ አፍሪካ አደገኛ ድርጅት እንዲመስል አድርጓል። በውጤቱም ምዕራቡ በምስራቅ አፍሪካ እና በቀይ ባህል ላይ ባሉት ጠቀሜታዎቹ የተነሳ እንዲሰጋ እና መለስ ዜናዊን ይበልጥ እንዲጠጋ አደረገ። ኢሳያስ አፈወርቂ በምዕራቡ ተኮነነ። ተከትሎም የተባበሩት መንግስታት በ2002 ዓመተ ምህረት በታህሳስ ወር አካባቢ ኢሳያስ አፈወርቂ በሶማሊያ የሚገኙ ሽብርተኞችን በማስታጠቅ እና በማሰልጠን ተግባል ተሰማርቷል ሲል ይከስ እና በኢሳያስ ኤርትራ ላይ እቀባ ጫነ። በዚህም ተጠቃሚው መለስ ዜናዊ ሆነ።

የሆነው ሆኖ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ከተተከለ ከኢትዮጵያ እየተነሳ በመላው የአፍሪካ ቀንድ አገሮች መናፈሱ አይቀርም። የአስመራው ኢሳያስ አፈወርቂ፣ የካርቱሙ ዑመር አል-በሺር እና የጅቡቲው አምባገነኖች እንዲሁም የመቅድሾ ኋላቀር አክራሪዎች ይህ የዲሞክራሲ ነፋስ ወደ ቀያቸው እንዲነፍስ አይፈልጉም። ስለሆነም በኢትዮጵያ ለሚካሄደው ሰላማዊ ትግል ወዳጆች እንደማይሆኑ ከወዲሁ መገንዘብ እና አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ይጠቅማል። ስለዚህ

## ምዕራቡ እና ምርጫ 2002፥

የአልቃይዳ ምስራቅ አፍሪካ ቅርንጫፍ አልሸባብ በምዕራቡ ዓለም ከተሞች ጥቃት እንዳይፈጽም፣ በሶማሊያ ታፍኖ እንዲቆይ የማድረጉን ተግባር ምዕራቡ በተለይ አሜሪካ ከዳግባዊ ብሹ መንግስት ጀምሮ ለመለስ ዜናዊ ኮንትራት ሰጥታቸዋለች።

የትጥቅ ትግል የመረጡ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶች በሶማሊያ እንዳይሰባሰቡ ከማድረግ ፍላጎቷቸው ጋር ስለሚጣጣም መለስ ዜናዊ ኮንትራቱን እጅ ነስተው ተቀብለው አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተዋል። መለስ ዜናዊ ለምዕራቡ በሰጡት ግልጋሎት የተነሳ የብዙ ወጣት ኢትዮጵያውያን ወታደሮች እሬሳ በሶማሊያ ሜዳ ሲጎተት አይተናል። እርግጠኛውን ምክንያት ለማወቅ የምርመራውን ውጤት መጠበቅ ተገቢ መሆኑ የተጠበቀ ቢሆንም በቅርብ ከቤይሩት አየር መንገድ እንደተነሳ በአየር ላይ ተበትኖ የብዙ ሰው ህይወት ጥፋት ምክንያት የሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ አደጋም ምክንያት ይኸው የመለስ ዜናዊ ግልጋሎት ስለመሆኑ በጉዳዩ ተጠርጥረው ከተያዙት ሰዎች ውስጥ የተናገሩ መኖራቸውም ተዘግቧል።

ከምዕራቡ የሚፈስላቸውን የኮንትራት ክፍያ እና ለልማት (ኢትዮጵያን ለማልማት) ምዕራቡ የሚለግሳቸውን ተጨማሪ ገንዘብ መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ለዲሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ለመግደል እየተጠቀሙበት ስለመሆናቸው አለም የሚያውቀው ነው። አለም አቀፍ ሰብዓዊ ድርጅቶች የዘገቡት ነው። አምኒስቲ ኢንተርናሽናል የዘገበው ነው። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይም በሪፖርቱ አመልክቷል። በአዲስ አበባ የተቀመጡ የእንግሊዝ፣ የአሜሪካ እና የአውሮፓ ህብረት የዲፕሎማሲ ቢሮዎች የሚያውቁት ሃቅ ነው። ምርጫ 2002ን አስመልክቶ  የወጣው የአውሮፓ ህብረት ጊዚያዊ ሪፖርት ሳይቀር የዘገበው ሃቅ ነው። ከዘገባው ውስጥ ለምሳሌ የፉክክሩ ሜዳ ሚዛናዊ አልነበረም፣ ገዢው ፓርቲ የመንግስት ንብረትን (ሃብትን) ለፖለቲካ ጥቅሙ ተገልግሏል፣ . . . በገዢው ፓርቲ እና በመንግስት ተቋሞች መካከል ሊኖር የሚገባው ግልጽ ልዩነት የለም ወይንም የደበዘዘ ነው . . . የሚሉ ወንጀይ ክሶች እንደሰፈሩ የምናውቀው ነው። የአውሮፓ ህብረት ሪፖርት ባጭሩ እና ጨዋነት በተሞላ ዲፕሎማሲያዊ መንገድ የዘገበውን በእግር ኳስ ቋንቋ እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል፥ “በኢትዮጵያ በ2002 የተደረገው የፖለቲካ ምርጫ ፉክክር (ግጥሚያ) በቅርቡ በደቡብ አፍሪካ የተካሄዱት የእግር ኳስ ግጥሚያዎች (ፉክክሮች) በገለልተኛ ፊሽካ በታጠቀ እና አራጋቢዎች ሲዳኝ እንደነበረው መዳኘት ሲገባው ፊሽካ በአፉ የሰካውም ሆነ በግራ እና በቀኝ መስመሮች የተተከሉት አራጋቢዎች በሙሉ ከአንደኛው ቡድን (የመለስ ዜናዊ ፓርቲ) የተመደቡ ነበር።”

በዚህ አይነት ነብዩ መሐመድ እና እየሱስ ክርስቶስ እንኳን 99.6 ከመቶ የህዝብ ድጋፍ በማያገኙባት ኢትዮጵያ መለስ ዜናዊ አገኙሁ አሉ። በመስቀል አደባባይ በጠሩት የድል አድራጊነት ህዝባዊ ስብሰባ መረጠኝ ላሉት ህዝብ 99.6 ከመቶ የህዝብ ድጋፍ ማግኘታቸውን ሲያበስሩት በታጠቁ ጠባቂዎች መታጀባቸው አንሶ በጥይት መከላከያ ሳጥን ተሸፍነው ነበር። በዚህ አድራጎታቸው ምንም ሳንደክም እራሳቸው በራሳቸው ለህይወታቸው ሳይቀር በሚፈሩት እና ምናልባትም 99.6 በመቶ በማይደግፏቸው (ባልመረጣቸው) ህዝብ መካከል ቆመው ንግግር በማድረግ ላይ መሆናቸውን ለአለም ህዝብ አስታወቁ። ድሉ የውሸት ድል ነበር። የተዘረፈ። በዚህ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ደግሞ የንግግራቸው አብዛኛው ይዘት የምርጫውን ውጤት ተቀበሉ የሚል መሆኑ መሳቂያ አድርጓቸዋል። በዚሁ ስብሰባ ላይ አለም አቀፍ የሰብዓዊ ድርጅቶችን ስም እየጠሩ ማውገዛቸው ደግሞ መንግስቱ ኃይለማሪያምን አስመሰላቸው።

## በሁለት መንግስታት መካከል የሚፈጠረ ግንኙነት ጸባይ፥

በሁለት መንግስታት መካከል የሚመሰረት ግንኙነት የጥቅም ግንኙነት ነው። ይህን ሃቅ ስንዘነጋ አሜሪካ ለምን በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ግንባታን አይረዳም ከሚል መገረም እንደርሳለን። በመንግስቶች መካከል የሚፈጠረው ግንኙነት በጥቅም ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ምዕራቡ የሚፈልገውን ጥቅም እስካገኘ ድረስ ከአባገነን ጋር ተወዳጀ አልተወዳጀ ብዙም የሚያስቸግረው ጉዳይ አይደለም። ምዕራቡ ጠዋት አምባገነኖች የሰሩትን በተጠማዘዘ እና መዘዋወር በበዛበት ዲፕሎማሲያዊ አነጋገር በመውቀስ የዲሞክራሲ የበላይ ጠባቂ ለመምሰል ይሞክራል፣ ከዚያ ከአምባገነኖች ጋር አብሮ ምሳ ይበላል፣ ለሊቱን ተቃቅፎ በማደር ጠቀሜታውን ያስጠብቃል።

በኢትዮጵያ ያሉት ዲፕሎማቶች በሙሉ ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ የሰብዓዊ መብት መከበር፣ ነፃ ፕሬስ፣ ዲሞክራሲ፣ ንግድ እና እርዳታ ያወራሉ። በኢትዮጵያ ሳሉ ግን በቅድሚያ በጽናት የሚሰሩት እና በየአገራቸው ላሉት አለቆቻቸው የሚዘግቡት በኢትዮጵያ ቆይታቸው የአገራቸውን ጥቅም በምስራቅ አፍሪካ ለማስጠበቅ ስለሰሩት ንግድ ነክ እና የስለላ ስራዎች እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ ሰብዓዊ መብት እንዲከበር ስለፈጸሙት እና ለዲሞክራሲ ግንባታ ስላበረከቱት አይደለም። ባጭሩ የማንኛውም አገር ዲፕሎማት ወደ ኢትዮጵያ ደሞዝ ተከፍሎ የሚላከው ለኢትዮጵያ ህዝብ ተብሎ እንዳልሆነ ግልጽ ነው።

## ከታሪካችን - ምዕራቡ እና ኢትዮጵያ፥

ስለምዕራቡ ከታሪካችን መማራም አለብን። ጥንት ዐፄ ቴዎድሮስ በመቅደላ እንዲሰዉ አድርጎ ኢትዮጵያን ያለመሪ ያስቀራት ምዕራቡ (እንግሊዝ) ቴዎድሮስ አልታዘዙ ስላሉት ነበር። ዐፄ

ዮሐንስን አጭበርብሮ በኢትዮጵያውያን ጀግኖች ደም የተጠቀመው እና በመጨረሻም በተጠማዘዘ ታሪካዊ ሁኔታ ውስጥ ዮሐንስን ወደ ሞታቸው የሸኘው (የሄዊትን ስምምነት እና ስምምነቱ ያስከተለውን ተመልከት/ች) ምዕራቡ (እንግሊዝ) ነበር። በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1868 ዓመተ ምህረት ዮሐንስ በጉንደት እና በጉርዓ የጀግንነት ሜዳዎች በግብጽ ላይ ያገኙዋቸውን ድሎች አስፋፍተው ግብጽን ከምጽዋ እንድትወጣ እና ምጽዋ ወደ ኢትዮጵያ እንድትመለስ እንዳያደርጉ ተቆርቋሪ ወዳጅ እና የቅርብ መካሪ መስሎ በስውር ግን ከግብጽ ጋር ተወዳጅቶ የምጽዋን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ያከላከለው ምዕራቡ (እንግሊዝ) ነበር። ምጽዋ ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ መግባት ሲገባት ለዮሐንስ ወዳጅ መስሎ ከጀርባ ግን ከኢጣሊያ ጋር ተመሳጥሮ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በጥር ወር 1877 ዓመተ ምህረት ኢጣሊያ ምጽዋን እንድትወር ያደረገው ምዕራቡ (እንግሊዝ) ለጥቅሙ ሲል ነው። በኋላም በታሪክ መረብ ምላሽ በመባል የሚታወቀውን የኢትዮጵያን ሰሜናዊ ክፍል ምዕራቡ (ኢጣሊያ) ከወረረች በኋላ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በታህሳስ ወር ማለቂያ 1882 (እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ጥር 1 ቀን 1990 - የፈረንጆች አዲስ አመት ቀን ) ዓመተ ምህረት ኤርትራ (ማለትም ቀይ አፈር ወይንም ቀይ የብስ) በሚል መጠሪያ እንድትሰይም ትብብር ያደረገው እና የኢትዮጵያን መረብ ምላሽ ኤርትራ በሚል መጠሪያ የኢጣሊያ ግዛት ነች ብላ ስታውጅ "አዎ! የኢጣሊያ ግዛት ናት!" የሚል እውቅና የሰጣት ምዕራቡ ለጥቅሙ ሲል ነው። ምዕራቡ ካፄ ምኒልክ የልጅ ልጅ ተቃዋሚዎች ጋር በስውር እና በይፋ ተመሳጥሮ ልጅ እያሱን (እያሱ አምስተኛው) ከስልጣን እንዲወገድ ያደረገው ምዕራቡ በኢትዮጵያ፣ በምስራቅ አፍሪካ እና በቀይ ባህር አካባቢ የነበሩትን ጠቀሜታዎች ተፈጻሚ ለማድረግ በወቅቱ በስልጣን ላይ የነበረው ልጅ እያሱ አስተማማኝ ወዳጅ መስሎ ስላልታየው ነበር። ስለዚህ ምዕራቡ ጥቅሙን አስተማማኝ በሆነ መንገድ ለማስጠበቅ የልጅ እያሱ የፖለቲካ ባላንጣዎች የቤት ዘመድ መካሪ በመምሰል እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በመስከረም ወር 1909 ዓመተ ምህረት የመስቀል በዓል እለት ልጅ እያሱ በሌሉበት የኢትዮጵያ መሪነት ስልጣን ከልጅ እያሱ ወደ ንግስተ ነገስት ዘውዲቱ እና ወደ አልጋወራሽ ተፈሪ ጥምር መንግስት እንዲሸጋገር ያደረገውን መፈንቅለ መንግስት ያቀናበረው ምዕራቡ ነው። ከሁለተኛው አለም ጦርነት በኋላ ኢጣሊያ በመሸነፏ ኢትዮጵያ (እነ አክሊሉ) በተባበሩት መንግስታት ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ እንድትመለስ ላቀረበችው ጥያቄ ከኢትዮጵያ እንዳትዋኻድ እና በምትኩ ቀድሞውኑ ለውድቀት በተዘጋጀ ፈደሬሽን እንድትቀላቀል ያደረገው ምዕራቡ (እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ ኢጣሊያ፣ ፈረንሳይ፣ ወዘ.ተ.) ነው። የቀድሞ ታሪካችንን በሚመለከት ስለምዕራቡ ብዙ መናገር ይቻላል።

የቅርብ ታሪካችንንም ብንመለከት ምዕራቡ በኢትዮጵያ የመንግስት ስልጣን ላይ እንዲቀመጥ የሚመኘው በኢትዮጵያ፣ በምስራቅ አፍሪካ እና በቀይ ባህር ጥቅሙን ለማስጠበቅ ይጠቅመኛል ያለውን የፖለቲካ ቡድን እንደሆነ እንረዳለን።

በ1883 ዓመተ ምህረት በለንደን ከተማ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስጠብቁ ህብረ ብሔር ፓርቲዎች በሌሉበት ህውሃትን፣ ሻቢያን እና ኦነግን ብቻ ሰብስቦ ስልጣን ከመንግስቱ ኃይለማሪያም ወደ እነዚህ ድርጅቶች እንዲሸጋገር ያደረገው ምዕራቡ ለጥቅሙ ሲል ነው። ወደ ስልጣን ለመውጣት እና በስልጣን ላይ ለመቆየት ያላቸውን ምኞት ተፈጻሚ ለማድረግ መለስ ዜናዊ ቀደም ብለው ኮምንስት ቆባቸውን አውልቀው በመደበቅ በነፃ ፋክክር እንደሚያምኑ አስመስለው መናገር በመቻላቸው የምዕራቡን ልብ በትንሽም ቢሆን ሳይማርኩ አልቀሩም። ፕሬዘዳንት ክሊንተን እና ጠቅላይ ምንስትር ቶኒ ብሌር በከፊል አምነውበት በከፊል ደግሞ ለወደፊት ታዛዦች እንዲሆኑ ለመኮትኮት ብለው በሚመስል ሁኔታ መለስን እና ኢሳያስ አፈወርቂን "የአፍሪካ አዲስ ትውልድ መሪዎች" የሚል ዘፈን አዘፍነውላቸው እንደነበር እናስታውሳለን።

በምርጫ 1997 ድምጻቸውን በሰላማዊ መንገድ ለማስከበር አደባባይ የወጡ ያልታጠቁ ዜጎችን የመለስ ዜናዊ መንግስት ግንባር ግንባራቸውን እያለ ቢገድልም፣ በሃሰት አገር የማጥፋት ክስ ወንጅሎ የሰላም ትግል መሪዎችን አፍሶ እስር ቤት ቢከትም፣ አለም አቀፍ የሰብዓዊ ድርጅቶች ድርጊቱን ቢኮንኑም፣ ድምጽ የመለስ ዜናዊ ፓርቲ የህዝብ ድምጽ መሰረቁ ቢታወቅም ምዕራቡ በምስራቅ አፍሪካ በሽብርተኛነት ላይ መለስ ዜናዊን ወዳጅ በምድረጉ በምርጫው ላይ የፈጸመውን ወንጀል ቸል በማለት ሳይወሰን የዳግማዊ ቡሽ መንግስት ይባስ ብሎ በ1997ቱ ምርጫ ተቃዋሚዎችን በጠብ ጫሪነት ወቀሰ። [ምርጫ 1997 ወደፊት በክፍሉ ታደሰ የተጻፈውን "ግንቦት 7" የሚለውን መጽሐፍ ተጠቅመን በሰፊው የምንገመግመው ታሪካችን ነው። ምርጫ 1997 ብዙ የምንማርለት ሰፊ ሃብት ሰጥቶናል።]

ምናልባትም ከመለስ ዜናዊ ጋር ስትነጻጸር ለኢትዮጵያ ጥቅም በጽናት የምትቆም ሰው መሆኗን በመገንዘብ ይሆናል ምዕራቡ የሰላም ትግል መሪዋ ብርቱካን መዴቅሳን መታሰር እያወቀ ካለምንም ምክንያት ካሰራት መለስ ዜናዊ ጋር መወዳጀቱን የመረጠው። አልፎም ብርቱካን ለታሰረችበት የጥበቃ ተቋም ሰራተኞች ሳይቀር ደሞዝ የሚከፈላቸው ከአሜሪካ፣ ከእንግሊዝ እና ከአውሮፓ ህብረት (ምዕራቡ) በእርዳታ ስም ለመለስ ዜናዊ ከሚፈሰው ገንዘብ ነው። በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትም ምዕራቡ መለስ ዜናዊን ከእነ ስየ አብርሃ የተሻለ አድርጎ የመረጠበት ምክንያት

የኢትዮጵያን ጥቅም የማያስጠብቀውን  የምዕራቡን የመፍትሄ አሳብ መለስ ዜናዊ በመቀበሉ እና እነ ስየ አብርሃ በመቃወማቸው ነው።

አሁንም ከምርጫ 2002 በኋላ እርዳታ እና ወዳጅነቱን ምዕራቡ አላቋርጠውጠም። የፕሬዘዳንት ኦባማ መንግስት በኢትዮጵያ በ2002 ምርጫ ድምጽ ተሰርቋል ማለት እንኳን አልደፈረም።

### ምዕራቡ - ከኢትዮጵያ ውጪስ?፥

ከኢትዮጵያ ወጣ ስንልም የተለየ አይደለም። ጉዳዩ ጥቅም ነው። እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1994 ዓመተ ምህረት በብሩንዲ በተከሰተው የሰው ዘር ፍጅት 800 ሺ ያህል ህዝብ ሲያልቅ ምዕራቡ (ክሊንተንም ሆነ ቶኒ ብሌር) እንዳላየ እና እንዳልሰማ የሆነው የሰብዓዊ መብት ሳይረገጥ ቀርቶ አይደለም። ምናልባትም ጣልቃ በመግባት የሚገኝ ጥቅም ስላልነበር ይሆናል። ሌላም ብዙ ማስረጃዎች መጥቀስ ይቻላል።

### በምዕራቡ አገር የገዢ ፓርቲ መቀየር እና የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አለመቀየር፥

ኦባማ (ፕሬዘዳንት) እንዲመረጥ ከጣሩት ኢትዮጵያውያን ውስጥ ጥቂትም ቢሆኑ በምላሹ ትንሽም ቢሆን ለኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክራሲ የሚጠቅም ነገር እናገኛለን የሚል ተስፋ እንደነበራቸው በአሜሪካ በተደረገው ምርጫ ሰሞን በቪኦኤ አማርኛ ፕሮግራም ቃለ ምልልስ ፕሮግራሞች የሚናገሩ ኢትዮጵያውያን አሜሪካውያን ነበሩ። አሳባቸው እና ምኞታቸው በጉ ነው። ቢሆንም ግን የውጭ ፖሊሲን በሚመለከት በሩፓብሊክ እና በዲሞክራሲ ፓርቲዎች መካከል ብዙም ልዩነት ባለመኖሩ ለኢትዮጵያ በጎ በመመኘት ለአባማ መመረጥ በርትተው ከሰሩት ኢትዮጵያውያን ውስጥ በምርጫ 2002 መለስ ዜናዊ 99.6 ከመቶ አሸነፍኩ ሲል የፕሬዘዳንት ኦባማ አስተዳደር ከቃላት ያለፈ ጥርስ ያለው እርምጃ ባለመውሰዱ ያልተደሰቱ ሊኖሩ ይችላሉ።

እርግጥ በግለሰብ ደረጃ ከዲሞክራሲ ፓርቲ የሆኑትን ኦባማን፣ ክሊንተንን፣ ሂለሪን ከሩፓብሊክ ፓርቲ ከሆኑት ከቡሽ እና ከዲክ ቼይኒ የተሻለ ልንወዳቸው እንችላለን።  ነገር ግን የአሜሪካን የውጭ ጥቅም በማስጠበቅ ረገድ ሁለቱም ቡድኖች አንድ እንደሆኑ መዘንጋት የለብንም። ልዩነት ካላቸውም የአቀራረብ፣ የአነጋገር፣ የአፈጻጸም እንጂ ከዚያ ባሻገር የሚሄድ አይሆንም።

ስለሆነም በአንድ አገር ገዢ ፓርቲ ተቀየረ ማለት የዚያ አገር የውጭ ጥቅሞች ተቀየሩ ማለት አይደለም። ስለዚህ የውጭ ፖሊሲውም አይቀየርም። ስለዚህ በኢትዮጵያ ለውጥ ለማምጥት ዋና ተስፋችን ህዝባችን መሆን አለበት። የእኛን የውስጥ ስራ ፕሬዘዳንት ኦባማ እንዲሰራልን መጠበቅ የለብንም። የአሜሪካ መንግስት ከአምባገነን መንግስት ጋር ተባብሮ በገንዘብ እየቀለበ ትግላችንን

እንዳይወጋ፣ የኢትዮጵያን ተቃዋሚ ትግል እንዳያዳክም፣ ኢትዮጵያ ለአሜሪካ መንግስት ጥቅም መጠበቅ በምትለግሰው አስተዋጽዖ ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ እና የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲያችም ባለቤትነት እንዳላቸው እና ተገቢው ክብር እና ትብብር ሊደረግላቸው መጠየቅ ግን እንችላለን።

## አዲሱ ዓለም (New World Order) – ምዕራቡ ቃሉን አለመጠበቁ፥

የበርሊንን ግንብ መፍረስ ተከትሎ የቀዝቃዛው ዓለም ጦርነት ዘመን ወደቀ ተብሎ ነበር። ከዚያም የሶሻሊዝም መውደቅ እና የአንድ ፓርቲ ስርዓት መውደቅ (ቢያንስ በአፍ ደረጃ) ዘመን ማብቃቱ በምዕራቡ ተለፍፎ ነበር። የካፒታሊስቱ ነፃ ፉክክር በአሜሪካ መሪነት በአለም የበላይነት መያዙ ታውጆ ነበር። ይኸ ማለት ደግሞ ነፃ ፉክክር፣ የሰብዓዊ መብት መከበሪያ፣ የነፃ ፕሬስ፣ የዲሞክራሲ ግንባታ እና የህግ የበላይነት መርሆዎች ተፈጻሚ የሚሆኑበት ዘመን ማለት እንደሆነ ተበስሮ ነበር። በዚህ አይነት  ዲሞክራሲ እንዲስፋፋ እና አምባገነንነት እንዲጠፋ የምዕራቡ ዓለም እንዲሁም የተባበሩት መንግስታት ማንኛውንም አይነት እገዛ (ገንዘብ ጨምሮ) እንደሚያደርግ ቃል ገብቶ ነበር። እንደሚታየው ግን ለእነዚህ መርሆዎች የከንፈር ግልጋሎት ከመስጠት ባሻገር ምዕራቡ ዛሬም እንደ ጥንቱ ከአምባገነኖች ጋር መተቃቀፉን ቀጥሏል። ምክንያቱም በሁለት መንግስታት መካከል የሚፈጠር ግንኙነት በጠቀሜታ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ምዕራቡ ጠቀሜታው እስከተጠበቀ ድረስ ከአምባገነኖች ጋር ተቻችሎ ለመኖር ይገደዳል።

**ምዕራቡ ከኢትዮጵያ ገዢዎች ጋር ሲወዳጅም ሲጣላም እንደቆየ እና የግንኙነቱን ጸባይ (መልክ) የሚቀይሰው ከጥቅሙ አኳያ እንደሆነ ከፍ ብለን ተመልክተናል። ሁልጊዜም ቢሆን ለምዕራቡ ቀዳሚ ወዳጁ ጥቅሙ ብቻ ነው።**

እርግጥ ዲፕሎማቶች ወዳጅና ሽምጋይ መስለው፣ የቤት ውስጥ ዘመድ እና መካሪ ሆነው፣ ተቆርቋሪ ወቃሽ ወይንም አዛኝ ሞጋች በመምሰል በፖለቲካችን ውስጥ በተዘዋዋሪ እና በይፋ ጣልቃ የገቡባቸው ጊዚያት እንዳሉዋቸው ከፍ ብለን ተመልክተናል። ይኸን የሚያደርጉትም በቅድሚያ ብዙ ከመከሩበት እና ያን ማድረግ ለራሳቸው ጥቅም አስፈላጊ ነው ብለው ሲያምኑ ብቻ ነው። ገዢው ፓርቲ አልታዘዝ ወይንም አልተባበር ካላቸው፣ ተቃዋሚ ፓርቲ ከገዢው ፓርቲ የተሻለ የሚታዘዛቸው ወይንም የሚተባበራቸው ከመሰላቸው፣ ተቃዋሚ ፓርቲ ለጥቅማቸው የተሻለ አማራጭ ከመሰላቸው፣ ተቃዋሚ ፓርቲ ታላቅ የህዝብ ድጋፍ እንዳለው ሲገነዘቡ፣ ለእነሱም ጥቅም እንቅፋት እንደማይሆን  ሲረዱ፣ ገዢው ፓርቲ (ኢህአዴግ) በ1997 እና በ2002 ምርጫዎች በተቃዋሚ ላይ የፈጸመው "ምርጫውን ነጻ፣ ግልጽ እና ሚዛናዊ ይሁን" በሚል

ወይንም ከምርጫ በኋላ የተዘረፈ ድምጽ ለማስመለስ "ድምጽ ይከበር" የሚል ብርቱ የህዝብ ተቃውሞ ሲቀሰቀስ ምዕራቡ ጣልቃ ይገባል።

ምዕራቡ ዘመዱ ጥቅሙ ብቻ በመሆኑ የዲፕሎማሲ ትግላችን ምዕራቡን በትንሹም ለመቆጣጠር የሚችለው የምዕራቡን ጥቅም ከስሌት ያስገባ ሲሆን ነው። አምባገነኖችም ምዕራቡን በማጭበርበር እየተካኑ እንደሚሄዱ መዘንጋት የለብንም። እሱም መጋለጥ አለበት።

## የኢትዮጵያ የሰላም ትግል በዲፕሎማሲው ግንባር፥

የዲፕሎማሲው ትግል ሙቀት ከፍ መደረግ አለበት። የዲፕሎማሲው ትግል ጽኑ፣ ብልህ እና ዲፕሎማሲያዊ መሆን ይገባዋል። የዲፕሎማሲ ትግላችን የምዕራቡን ጥቅም ያስተዋለ እና በምዕራቡ ጥቅም ላይ የሚወያይ እና የሚያወያይ መሆን አለበት። የዲፕሎማሲው ትግል ምዕራቡ ለገዢው ፓርቲ የሚረጨው ገንዘብ የሰላም ትግልን እና የዲሞክራሲ ግንባታን ለማዳከም በመዋሉ ምዕራቡን በዲፕሎማሲያዊ አነጋገር በኋላፊነት የሚጠይቅ መሆን አለበት። የዲፕሎማሲ ትግላችን የአፍሪካ አምባገነን መንግስታት ንድፈ አሳብ አቀንቃኝ እና አውጠንጣኝ ምሁራን የሚፈጥሩዋቸውን የማጭበርበሪያ ንድፈ አሳቦች የሚታገል እና የሚያሸንፍ መሆን አለበት። የዲፕሎማሲ ትግላችን ከዲፕሎማቶች ጋር ቅርርብ ያለው፣ ከዲፕሎማቶች የሚሰማ እና በዲፕሎማቶች የሚደመጥ ትግል መሆን አለበት። የዲፕሎማሲው ትግል ምዕራቡን የሚያስተምር እና ደጋፊ የሚያደርግም መሆን አለበት። ምዕራቡን ዛሬም ሆነ ወደፊት በአስተማማኝ ተጠቃሚ የሚያደርገው ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር (በተቃዋሚ ፓርቲም በኩል) የሚያደርገው መወዳጀትም እንጂ 99.6 ከመቶ አሸነፍኩ እያለ እራሱ በጠራው ህዝብ ፊት በጥይት መከላከያ ሳጥን ውስጥ ቆሞ ከሚናገር መሪ ጋር ብቻ በሚያደርገው መወዳጀት እንዳልሆነ በዲፕሎማሲያዊ አነጋገር ምዕራቡ አለም እንዲገነዘብ መደረግ አለበት። በምስራቅ አፍሪካ ሽብርተኞችን የሚታገለው የኢትዮጵያ ወጣት እንዲሁም ሰብዓዊ መብታቸው እየተረገጠ በየእለቱ የሚበሳጩ የኢትዮጵያ ወጣት እናት እና አባት እንጂ የኢህአዴግ ባለስልጣናት እንዳልሆኑ ምዕራቡ እንዲያጤነው መደረግ ያለበት ይመስለኛል። ምዕራቡ የሚሰራውን የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሚያስተውል ምዕራቡ በምር እንዲያውቅ መደረግ አለበት። እነቡርቱካንን እና የመድረክ መሪዎችን ቸል በማለት ምዕራቡ ከመለስ ዜናዊ ጋር ብቻ ተቃቅፎ መተኛቱን የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሚያስተውል እና እንደማያስደስተው ምዕራቡ ሊያውቅ ይገባል። የኢትዮጵያ ህዝብ ሽብርተኛን ለመዋጋት የሚለግሰው ትብብር መጠን ቋሚ እንዳልሆነ እና መጠኑ ከፍም ዝቅም ሊል እንደሚችል አልፎም ዜሮ ሊሆን እንደሚችል ምዕራቡ ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ እንዲገነዘብ በደረግ አለበት።

በጥቅሙ መሳካት ላይ ተቃዋሚውም ባለቤትነት እንዳለው በዲፕሎማሲያዊ አነጋገር በማሳወቅ ምዕራቡ ስጋት እንዲያድርበት ማድረግ ስንችል ነው። በዚህ ረገድ በራስ መተማመን ካለ፣ በሚሰሩት ስራ እምነት ካለ፣ በጽናት እና በብልህነት ከተሰራ የተሳካ ውጤት ማምጣት ይቻላል።

የዲፕሎማሲው ትግል ሙቀት ከፍ መደረግ አለበት። ለምሳሌ ያህል በሚከተሉት እና ሌሎች ተጨማሪ ጉዳዮችን እያነሱ ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻዎች ማድረግ የሚጠቅም ይመስለኛል።

(1) ኢህአዴግ በምርጫ ጊዜ እና በምርጫዎች መካከል ባሉት አምስት አመቶች ውስጥ የሚፈጽማቸው በዲሞክራሲያዊ መንግስት መለኪያዎች ሲሰፈሩ ኢህአዴግ አምባገነን እንጂ ዲሞክራሲያዊ አለመሆኑ የሚከተሉትን መስፈርቶች በመጠቀም ካለ መታከት ለምዕራቡ ማስተማር ይገባል። እርግጥ ምዕራቡ እያወቀ የማያውቅ ሊመስል ይችላል። ያ መሆኑ ግን ሊያቆመን አይገባም። ያ መሆኑ ተስፋ ሊያስቆርጠን አይገባም፥

(ሀ) ኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ካለምንም ወከባ በነፃነት መፎካከር የሚችሉባት አገር እንዳልሆነች በመረጃ እያስደገፉ ካለምንም መታከት ምዕራቡ እንዲያውቅ መወትወት። (ለ) ህዝቡ ካለምንም መዋከብና እንግልት ድምጽ መስጠት እንደማይችል በማስረጃ አስደግፎ ማስታወቅ፣ (ሐ) በስልጣን ላይ ያለው ገዢ ፓርቲ ስልጣኑን በእጁ ያቆየው በህዝቡ ፈቃደኝነት ሳይሆን የህዝቡን ድምጽ በመስረቅ እና ህዝቡን በፍራቻ በመግዛት እንደሆነ መግለጽ፣ (መ) ገዢው ፓርቲ የአንድ ፓርቲ የፖለቲካ ስርዓት አማኝ እንደሆነ በመግለጽ ገዢው ፓርቲ ቢሸነፍ የህዝብ ውሳኔ አክብሮ በመቀበል ሰላማዊ የመንግስት ሽግግር የማድረግ የፖለቲካ ባህል እንዳልነበረው እና መማርም እንደሚያስቸግረው፣ (ሠ) አብዮታዊ ዲሞክራሲ የሚለው የኢህአዴግ መመሪያ ዲሞክራሲ የለም ማለት እና ከስልጣን አልወርድም ማለት እንደሆነ ማሳወቅ፣ (ረ) ገዥው ፓርቲ በስልጣን ዘመኑ የህዝብን በነፃነት የመናገር፣ ስለአገሩ አቅጣጫና አመራር ድምጹ የመሰማት፣ በህግ የበላይነትና ፍትሃዊ አስተዳደር ስር እንዲስተዳደር የመፈለግ መብት በማክበር በመቻቻልና በድርድር ህዝብን የሚገዛ ሳይሆን በፍራቻና በግድያ የሚገዛ እንደሆነ በማስረጃ እያስደገፉ ማቅረብ፣ (ሰ) ገዢው ፓርቲ ለህዝብ ግልጽ እንዳልሆነ፣ የህዝብ ድምጽ እንደሚሰርቅ እና ህዝቡ በመረጠው መንገድ እንዲኖር የማይፈቅድ መንግስት መሆኑን፣ እና (ሸ) ገዥው ፓርቲ በስልጣን ዘመኑ የህዝቡን ጠቀሜታና ህጋዊ የፖለቲካ ሂደት ተግባር ከፓርቲው ማስቀደም የተሳነው እና የአገሪቱን እና የመንግስትን ሃብት እንዲሁም ተቋም ለፖለቲካ ፓርቲው ጠቀሜታ እንደሚያውል በማስረጃ መግለጽ ያስፈልግ ይሆናል።

(2) ከለጋሽ አገሮች ለልማት የተለገሱ የእርዳታ ገንዘቦች አጠቃቀምን አስመልክቶ በተቻለ መጠን ምን ያህል ለልማት እንደተለገሰ፣ ከዚያ ውስጥ ምን ያህሉ ለልማት እንደዋለ እና ምን ያህሉ ኢህአዴግን በስልጣን ላይ ለማቆየት ለሚያስችሉ የተለያዩ ተግባሮች እንደዋለ ዝርዝር የሂሳብ ገቢ እና ወጪ ተዓማኒ መረጃ የያዘ ሰነድ በጥንቃቄ በማዘጋጀት መንግስትን በአለም ህዝብ ፊት በሙስና ማጋለጥ እና በአደባባይ መክሰስ ያስፈልጋል። ስለዚህ የዲፕሎማሲው ትግል ትክክለኛ መረጃ በጥንቃቄ ከማስረጃዎች ጋር በማሰባሰብ ሙስናን ማጋለጥ እና ሌሎች ህጋዊ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል።

የፖለቲካ መሪዎች በስልጣን ላይ ለመቆየት ሲሉ ብቻ ለአገሪቱ ልማት የተለገሱ ብሮችን ለካድሬዎቻቸው፣ ለጸጥታ እና መረጃ ቅጥረኞቻቸው፣ ለቪኦኤ አማርኛው ስርጭት ማፈኛ፣ የተቃዋሚ ፓርቲ ቢሮዎች የውጭ ግንኙነቶችን ለመሰለል፣ የሃሰት ክስ እየመሰረቱ ለፍትህ ምኒስትር ሰራተኞች የሚከፍሉት ከሆነ በእዚያች አገር ልማት አይኖርም። አገር ከድህነት አትወጣም። ገዢዎች እራሳቸውን ለማክበር ኢኮኖሚውን የሚበዘብዙ ከሆነ አንድ አገር ሃብት ልታፈራ አትችልም። ሙብት የማይከበር ከሆነ ሰው ነፃነት ተሰምቶት በሙሉ ልቡ ስለማይሰራ ማንም በእንደዚያ አይነት አገር ኢንቨስት ማድረግ አይፈልግም። ይህ ሁሉ እያለ የይስሙላ ምርጫ ስለተደረገ ብቻ በዚህ አይነት አገር ውስጥ ዴሞክራሲ አለ ማለት አይቻለም። ያለው ዴሞክራሲ ሳይሆን አምባገነንነት ነው። ይህን አይነት አገዛዝ በአፍሪካ የተለመደ ነው።

(3) ዲሞክራሲ ሲነሳ ሉዓላዊነትን እንደመከላከያ ማንሳት የአምባገነኖች የተለመደ ዘዴ መሆኑ ሊጋለጥ ይገባል፥

ምዕራቡ ስለ ዲሞክራሲ ባነሳ ቁጥር የአፍሪካ አምባገነኖች በሉዓላዊነት ጣልቃ ገባችሁ በማለት ምዕራቡን እንዲሸማቀቅ ያደርጋሉ። ይኸ የአምባገነኖቹ አድርባይ ምሁራን የፖለቲካ አቀንቃኞቻቸው የፈጠሩላቸው ማስፈራሪያ ነው። በዲሞክራሲ ጉዳይ ምዕራቡ ጣልቃ ገባ ሊባል የሚቻለው ገዢው ፓርቲ ብቻ ስለጮኸ አይደለም። የተቃዋሚ ፓርቲዎችም አቅዋም መታወቅ አለበት። የተቃዋሚ ፓርቲዎች ድምጽም መሰማት እንዳለበት በሰፊው እንዲታወቅ በማድረግ አምባገነኖች በዲሞክራሲ ጥያቄ ሲተቹ የሚከፍቱት በሉዓላዊነት የተሸፈነ ጦርነት እንዲገታ ማድረግ ያስፈልጋል።

(4) ዲሞክራሲ ከውስጥ ይበቅላል እንጂ ከውጭ አይጫንም በማለት እነ መለስ ዜናዊ ምዕራቡን ለማደናገር የሚያደርጉት ሙከራ የአፍሪካ አምባገነኖች ማጭበርበሪያ መሆኑ በግልስ እና በሰፊው መጋለጥ አለበት፥

የህዝባቸውን ድምጽ የማያደምጡ የአፍሪካ መንግስቶች ምዕራቡን ገንዘቡን ብቻ ግፉ እንጂ እንዴት እንደምንጠቀምበት አትንገሩን የሚለው ሙግት የመለስ ዜናዊ ሙግት ነው። ዲሞክራሲ ከውስጥ ይመነጫል እንጂ ከውጭ አይጫንብን የሚለው አሳባቸው ተቀባይነት እንዲያገኝ ምዕራቡ እርዳታ በመስጠቱ ብቻ እንደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተሰለፉ ባይሉን ይሻላል እያሉ መሰሎቻቸውን የአፍሪካ አምባገነኖች ያስተባብሩ ነበር። በዚህ መልኩ መለስ ዜናዊ የአፍሪካ ደደብ አምባገነኖች ንድፈ አሳብ መሪ ይመስላሉ። ልክ ጥንት በውንጌት ትምህርት ቤት በስውር ያደርጉት እንደነበረው አሁንም የአፍሪካ አምባገነኖችን አንዳንዴ በምዕራቡ ላይ በስውር ሳያስተባብሩ አይቀሩም።

ስለዚህ "ዴሞክራሲ ከውስጥ ይበቅላል ከውጭ ይጠጣል" የሚለው አባባል ማጭበርበሪያ እንደሆነ መጋለጥ ይኖርበታል። አምባገነኖች ምዕራቡ እርዳታን ከዴሞክራሲ ጋር እንዳያስተሳስረው ለማድረግ እና የዕርዳታውን ገንዘብ ስልጣናቸውን በማጠናከር እስከ ልጅ ልጆቻቸው ድረስ ከስልጣን ላለመውረድ የሚያደርጉት ጥረት እንደሆነ መጋለጥ አለበት። ምዕራቡ በአፍሪካ ዴሞክራሲ እና በምርጫ ጉዳይ ጣልቃ ሳይገባ ብሩን ብቻ ይግፋ ማለታቸው መሆኑ መጋለጥ አለበት።

እርግጥ ነው ዲሞክራሲን ለማራመድ ተብሎ የውጭ መንግስት ዲሞክራሲን በትዕዛዝ ሊጭን አይችልም። የሉዓላዊነትም ጥያቄ አለና መሞከርም አይኖርበትም። እርግጥ ነው የእያንዳንዱ አገር ህዝብ የራሱ ወግና

ተለምዶዎች ስላሉት ለዴሞክራሲ መርሆዎች በአገሩ ህይወት የሚሰጥበትም የራሱ መንገዶች ይኖሩታል። ስለዚህም ስለማዊ ምርጫ ሲባል ትንሽም ቢሆን ከህዝብ ህዝብ ከአገር አገር አንፃራዊነት የሆነ ልዩነት ሊኖረው ይችላል። ስለዚህ በአሜሪካ የሚታየውን የምርጫ ስርዓትና የዴሞክራሲ ባህል ፎቶግራፊያዊ ግልባጩን በኢትዮጵያ መጠበቅ እንደሌለብን ግልጽ ነው። ይህ ማለት ግን በመላው አለም የሚኖር ህዝብ በነፃነት መናገርን፣ ስለአገሩ አቅጣጫና አመራር ድምጹ እንዲሰማ፣ በህግ የበላይነትና ፍትሃዊ አስተዳደር ስር እንዲስተዳደር፣ መንግስቱ ግልጽና የማይሰርቀው እንዲሆንና በመረጠው መንገድ የመኖር ነፃነት እንዲኖረው መፈለግ የመላው ሰብአዊ ፍጡር የጋራ ፍላጎት አይደለም ማለት አይደለም። እነዚህ የኢትዮጵያ፣ ወይንም የአሜሪካ፣ ወይንም የጀርመን ወይንም የደቡብ አፍሪካ ህዝብ ብቻ ፍላጎቶች አይደሉም። የመላው ሰው ልጅ ፍላጎቶች ናቸው። ሁሉም መንግስቶች ሊቀበሉና ሊፈጽሟቸው የሚገቡ የሁሉም ሰው ዘር መብቶች ናቸው። በአለም ላይ ያለው የሰው ልጅ ሊደግፉቸው የሚገቡ መብቶች ናቸው። ስለዚህ ዴሞክራሲ ከውስጥ የሚበቅል እንጂ ከውጭ የሚጫን አይደለም የሚለው የአፍሪካ ጨቋኝ ገዢዎች አሳብ አጭበርባሪ አሳብ ነው። ስለሆነም የትም አገር ቢሆን እንዚህን መብቶች የሚረግጡ መንግስቶችን የአለምን ህብረተሰብ ድጋፍ ማግኘት የለባቸውም። እነዚህ መንግስቶች የህዝብን ምኞት አከባሪዎች አይደሉምና የአለምን ህዝብም ሊያከብራቸው አይገባም። የአለም ህብረተሰብ የሚጠበቅበት እጁን አጣምሮ መቀመጥ፣ አይኑን ጨፍኖ መሄድ ሳይሆን በእጁም፣ በአንደበቱም፣ በገንዘቡም የህዝብ ድምጽ እንዲያከብሩ ማደረግ አለበት። ጨቋኞች፣ ህዝባቸውን የማያከብሩ፣ ህዝባቸውን በፍራቻ የሚገዙ የአፍሪካ መሪዎች በማንኛውም ዴሞክራሲ ወዳድ ህዝብ መወቀስ አለባቸው። መወገዝ አለባቸው። ይባስ ብሎ ዛሬ አለም አንድ መንደር ሆናለች። ስለሆነም ዴሞክራሲ ከውስጥ ነው የሚበቅለው የሚለው የጨቋኞች ክርክር ታሪክም አልረዳውም።

(5) አፍሪካ ከዲሞክራሲ፣ ከሰብዓዊ መብት፣ ከነፃ መረጃ ይልቅ ሆዱ እንደሚቀድምበት እኛ እናውቃለን የሚለው የአምባገነኖች ፕሮፓጋንዳም መወገዝ አለበት። በማስረጃ እያስደገፉ ይህ አባባል ስህተት መሆኑ መጋለጥ አለበት። የአፍሪካ አምባገነኖች ለስልጣናቸው ሲሉ በቀጠሩዋቸው አድርባይ አፍሪካውያን ምሁራን ወይንም የምዕራቡ ዓለም ዘረኞ ሹማምንት ምሁራን የሚያሰራጩት አደገኛ ፕሮፖጋንዳ እንደሆነ መጋለጥ አለበት።

(6) የተሳሰርን በመሆናችን በኢትዮጵያ የአምባገነን መንግስት በስልጣን ላይ መቆየት የተነሳ ኢትዮጵያ ብትወድቅ የመጀመሪያው ተጎጂው የኢትዮጵያ ህዝብ ቢሆንም የምዕራቡ ዓለም ህዝብ ከችግሩ ብዙ የራቀ አለመሆኑን እንዲገነዘብ ማድረግ ያስፈልጋል፥

ዛሬ ሜክሲኮ ወይንም ሆንግ ኮንግ ለገባ የወፍ በሽታ በኢትዮጵያ አሳብ ይገባናል። የተሳሰርን በመሆናችን። የአለም ህብረተሰብ የተሳሰረ ነው። ኢትዮጵያ የሚደርሰው ውድቀት የምዕራቡን ዓለም በስደተኛ ሊሞላው እንደሚችል እና የምዕራቡ ህብረተሰብም ኢኮኖሚ መሸከም ከሚችለው በላይ እንዲሸከም ሊደረግ የሚችልበት ሁኔታ እና ተከትሎት ሊመጡ የሚችሉትን ችግሎች በመተንተን ምዕራቡ ከኢትዮጵያ አምባገነን መንግስት ጋር የሚያደርገው መተቃቀፍ የሚጎዳው የኢትዮጵያን ህዝብ ብቻ ሳይሆን ምዕራቡንም እንደሆነ እንዲሁም ሽብርተኛነት እና የመሳሰሉት ችግሮች መንስዔያቸው ተስፋ መቁረጥ እንደሆነ ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ ምዕራቡ እንዲገነዘብ መደረግ አለበት።

(7) ለፍትህ ሲባል መረጋጋት መናጋት የለበትም የሚለው የእነመለስ ዜናዊ ንድፈ አሳብ አጭበርባሪነቱ፣ አምባገነንነቱ እና ለህግ ያለው ንቀት በግልጽ መጋለጥ አለበት።

የሱዳኑ መሪ ዑመር አል-በሽር በጦር እና ህዝብ ፍጅት አለም አቀፍ ፍርድ ቤት ክስ ሲመሰርትባቸው እና ተይዘው ለፍርድ እንዲቀርቡ በተጠየቀበት ሰሞን እነመለስ ዜናዊ እርምጃውን ለመቃወም ያቀረቡት ንድፈ አሳብ ነበር። የአለም ፍርድ ቤት ወኪሎች ያልነበረ መረጋጋት አይናጋም በማለት የእነ መለስን ሙግት በወቅቱ ውድቅ አድርገውት ነበር። ቢሆንም ግን ውስጥ ውስጡን አሳቡ ሲሰራጭ ቆይቶ በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት የሚፈለግን ግለሰብ ይዞ ለማስረከብ የፈረሙ አገሮች ሳይቀሩ እንዲያምጹ ተደርገው በቅርቡ የሱዳኑ ፕሬዘዳንት ቻድን ሲጎበኙ የቻድ መንግስት አስሮ ለአለም አቀፍ ፍርድ ቤት ማስረከብ ሲገባው አላደረገም። የአለም አቀፍ ሰብዓዊ ድርጅቶች የቻድን መንግስት ቢማጸኑም የሱዳኑ መሪ ምንም ሳይደርስበት ጉብኝቱን ጨርሶ ወደ ሱዳን ተመልሷል። ይኸ ሁኔታ በሰፊው መጋለጥ አለበት።

(6) በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ግንባታ መታፈኑ - ከምዕራቡ የሚፈሰውን የገንዘብ እርዳታ ሚና በመግለጽ፥

በኢትዮጵያ ምርጫ ነፃና ግልጽ እንዳልሆነ፣ ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አለመሆኑ፣ የምርጫ አስፈጻሚዎች የመንግስት ካድሬዎች መሆናቸው፣ ገለልተኛ የአገርና የውጭ ታዛቢዎች በስፋት እንዲሳተፉ አለመፈቀዱ፣ ዴሞክራሲያዊ ተቋሞች (ነፃ ህግ አውጪ፣ ነፃ ፍርድ ቤት፣ ነፃ የዜና ማሰራጫ) እንዳይኖሩ መደረጉ፣ ነፃ የሲቪክ (የሙያ፣ የጾታ፣ የሰብዓዊ መበት ወ.ዘ.ተ.) ማህበራት እንዳይመሰረቱ፣ የተመሰረቱትም እንዳይጠናከሩ መደረጋቸው እና በአገራቸው የፖለቲካ እጣ ፈንታ ሚና እንዲኖራቸው አለመደረጉ በሰፊው ሊጻፍበት ይቻላል። ይኸን በማድረግ ምዕራቡን ማስተማርም፣ መፈታተንም፣ ምዕራቡ በሚለግሰው ገንዘብ እና ገንዘቡ ለካድሬዎች እና ለሰላዮች እንዲሁም ብቃት ለሌላቸው ወገንተኛ ሹሞች እየፈሰሰ በዲሞክራሲ ግንባታ ላይ በሚያደርሰው የማቀጨጨ ብሎም የግድያ ሚና በዲፕሎማሲያዊ አነጋገር ምዕራቡን በሞራል ኃላፊነት መጠየቅ ይገባል።

በዚህ ረገድ በቅርቡ የሚከተሉትን ሁለት ወይንም ሶስት ጽሁፎች ተመልክቻለሁ። [Steel vises, clenched fists and closing walls - Part I July 20, 2010 and Part II July 26, 2010 By Alemayehu G. Mariam **እና** The West's lofty rhetoric and dangerous miscalculations, By Andualem Aragie | July 26, 2010] በዚህ በዲፕሎማሲ ግንባር መደረግ ስላለበት ሰፊ አዲስ ዘመቻችን እነዚህ ጽሁፎች ጠቃሚ አጻጻፎች ይመስሉኛል። ጥሩ ጅማሬዎች ይመስሉኛል። አለመታከት ነው።

የዲፕሎማሲ ትግላችንን ግለት ከፍ ለማድረግ እና በሰፊው ለማዳረስ ምናልባትም የተለያዩ ታዋቂ የህትምት እና የድህረ ገጽ ሚዲያዎች በሰፊው መጠቀም አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ኢትዮሚዲያን ሳንዘነጋ ሌሎች በዲፕሎማቶች፣ በፖለቲካ አሳብ አቀንቃኝ ምሁራን፣ በሰብአዊ ድርጅት ተንቀሳቃሾች በሚዘወተሩ ድህረ ገጾች እንዲሁም ዋሽንግተን ፖስት እና ኒዎርክ ታይምስ አሜሪካ፣ ግሎብ አንድ ሜይል (ካናዳ) እንዲሁም በእንግሊዝ እና በአውሮፓ ሌሎች ታዋቂ ጋዜጦችን መጠቀም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። የሚላኩት ጽሑፎች ተቀባይነት አግኝተው ለህትምት

መብቃታቸው እራሱ የዲፕሎማሲ ትግላችን አካል ነውና ካለምንም መታከት ጥረት መደረግ ያለበት ይመስለኛል።

## የኢትዮጵያ ሰላማዊ ትግል ዋስትና ሰጪ ኢትዮጵያውያን ብቻ ስለመሆናቸው፥

ዋናው የሰላም ትግል ግን በእራሳችን ትከሻ ላይ መቀመጥ አለበት። ተቃዋሚው አንድነቱን አጠንክሮ የተሻለ አማራጭ ሆኖ መታየት መቻል አለበት። የወረቀት ላይ መግለጫዎች በማውጣት ብቻ ሳይወሰን ተጨባጭ ለውጥ የሚያመጡ ሰላማዊ ትግሎች በማድረግ ተከታይ እና የህዝብ ድጋፍ እንዳለው ለአለም ማሳየት አለበት። ተቃዋሚው በተጨበጭ ለምዕራቡ ዓለምም የተሻል አማራጭ ሆኖ በተግባር መታየት እና ክብርን በስራዎቹ ማግኘት መቻል አለበት።

**ለነፃነት ሲባል፣ ለዲሞክራሲ ግንባታ መሳካት ሲባል፣ ለህግ የበላይነት ድል አድራጊነት ሲባል መኢአድ ነፃነቱን እንደቀሩት አባል ድርጅቶች ጠብቆ በፍጥነት የመድረክ አባል ድርጅት በመሆን ትግሉን ማጠናከር አለበት እንላለን።**

በመጨረሻ የሚቀጥለው ጽሑፌ የሰርቢያ ህዝብ ከአንድ ፓርቲ ወደ መደብለ ፓርቲ ስርዓት የተሸጋገረበትን ሰላማዊ ትግሎች፣ ያደረጋቸውን ምርጫዎች እና ድምጽ ለማስከበር ያደረጋቸውን ስኬታማ ሰላማዊ አመጾች እንነበኛለን። እስከዚያ ድረስ መልካሙን እመኛለሁ።

የሰላም ትግል መሪዋ ብርቱካን መዴቅሳ ትፈታ! ሌሎችም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!

## ቀደም ብለው በኢትዮሚዲያ ድህረ ገጽ የቀረቡ ጽሑፎች

(1) የአሳብ ልዩነት
(2) መድረክ ታሪክ ሰርቷል፣ እድል እንስጠው
(3) የምርጫ ታሪካችን እና የወደፊት መንገዳችን
(4) በምርጫ 2002፣ መለስ እና መድረክ
(5) መንገዳችን!
(6) ሴቶች ለሰላም ትግል ያላቸው ልዩ ተሰጥኦ
(7) የታላቁ እያሱ ስኬታማ የሰላም ትግል በኢትዮጵያ
(8) መፈንቅለ መንግስት ያስወገደ እና የህዝብ ድምጽ ያስከበረ የሰላም ትግል ስትራተጂ (በርሊን)
(9) ከማርቲን እና ከሮዛ ፓርክስ ሰላማዊ አመጽ የምንማረው